# ሽቅብ መሮጥ ሲሳንህ - ቁልቁል ተንደርደር

ታሪኩ አባዳማ   ግንቦት 2001

የትችቴ ርዕስ የተወረሰው ከኦሮምኛ ተረት ነው፦ “ኦል ካቼ ዮደደብዴ ገዲ ካዱ” ከሚለው። በአማርኛ አቻ ትርጉም ሊሰጥ የሚችል ብሂል ቢኖር ብዬ ሳፈላልግ ብዙ ቀናት ፈጅቶብኛል። ትርጉሙ ወደ ኋላ ይቆየኝና ለትችቴ መነሻ ወሆነኝ ጉዳይ ልውሰዳችሁ። ጉዳዩ ሲብራራ ተስማሚውን ትርጉም እናንተው ትሰጣላችሁ። በቅርቡ ከወደ ካናዳ/ቶሮንቶ ‘መኢአድ/ቅንጅት’ በሚል ሥም የሚንቀሳቀስ ቡድን ያሰራጨው ‘የድል’ ዜና ለዚህ አጭር አስተያት መነሻ ሆኗል። በመሠረቱ ‘መኢአድ/ቅንጅት’ የሚባል ድርጅት በአገርም ሆነ በውጭ ተቋቁሞ የነበረ መሆኑን እስከዛሬ አልሰማሁም። ቅንጅት በድርጅቶች ውህደት እንደ አንድ የፖለቲካ አካል ሲመሰረት መኢአድ የሚል ጉትያ እንዳልነበረው ግን ሁሉም ያውቃል። ቅንጅት የድርጅቶችን ግርግዳ አፍርሶ ከጠባብ የድርጅት ስሜት እና ከአምልኮ ግለሰብ የዘለለ አቋም መከተል ብቸኛ መድኀናችን መሆኑን ያመለከተ ጎዳና ነበር - እናም ቅንጅት ሌላ መኢአድ ሌላ። ቶሮንቶ ላይ ድል በተጎናፀፉት መኢአድ እና ባጃቢዎቻቸው ይቅርታ ይደረግልኝና ያበቀሉትን የቅንጅት ቁንጮ በጨዋ ደንብ ቢላጩት መልካም ይመስለኛል። ስለተስተጋባው ‘ድል በድል’ ፈንጠዝያ ግን ጥቂት እንድል ይፈቀደልኝ።

ቅንጅት ባጭር የፖለቲካ ዕድሜው ዘለግ ያለ የፖለቲካ ተውኔት የቀረበበት መድረክ ነበር። ሰኞ - ፍትህ እና ሰላምን መጎናፀፊያው በማድረግ ተፀንሶ ፤ ማክሰኞ - በመላ ዜጎች ብያኔ ድል አድርጎ ፤ ረቡዕ ጎልምሶ ፤ ሐሙስ ተከሶ ፣ አርብ በወያኔ ስቅላት ተፈርዶበት ፣ ቅዳሜ ሳይሰቀል በፀና ታሞ እሁድ እንደ ፖለቲካ አካል በገዛ እጁ የሞተ - በመፀነሻው የሰረፀው መንፈስ ግን  በዜጎች ልቦና ውስጥ ያደረ የፍትህና የነፃነት ሰንደቅ ነው። ሁሉም ነገር በጥድፊያ የተከናወነበት ፣ ግራ ቀኙን መዝኖ እና ተረጋግቶ እርምጃን ለመቀየስ ፋታ ፣ ትንፋሽ የጠፋበት አገርን ከጎጠኛ የማዳን ሩጫ። ትልቁ ስዕል ላይ ያተኮሩ ጠንካራ እና በሳል ዜጎች ከማን ጋር እንደተሰለፉ እንኳ ማጤን ያልቻሉበት ፤ በወጉ ለመሞት ግዜ የጠፋበት - እጥር ምጥን ያለ የፖለቲካ ትራጀዲ።

ትራጀዲው በብዙ ገፀ-ባህርያት የታጀበ ነበር። ቅንጅት በፅንሰቱ ያስተጋባው የግልፅነት እና ተጠያቂነት መርሆ ተረግጦ በድብብቆሽ ሤራ ተጎንጉኗል ፣ ቅን ዜጎች ለድጋፍ ያበረከቱት ንዋይ እንደ ዋዛ ተዘርፏል፣ ድርጅታዊ ሥርዓትና ደንብ አይገዛንም ያሉ አዜዎች በቅለዋል ፣ በትግል አጋራነት የቆሙ ዜጎች ሃላፊነት በጎደለው ቋንቋ ሳይቀር ሲወገዙ እና ሲወረፉ ታዝበናል። ይህ ሁሉ በዓይናችን ሥር ሲፈፀም ማየታችን አልበቃ ብሎ ቅንጅትን ለሞት ያበቁ ያዜው ሎሌዎች የቅንጅትን ስም እንደ ቁንጮ ሊጠቀሙበት መድፈራቸው የቅንጅትን መንፈስ በልቦናቸው ባኖሩ ሚሊዮን ዜጎች ዘንድ ሀዘን መፍጠሩ አይቀርም።

ያ የቅንጅት መንፈስ፦ የአንድነት ፣ የግልፅነት ፣ የተጠያቂነት ፣ የሥርዓትና-ደንብ የበላይነት መረጋገጥ ጥያቄ ጎጠኞችን እንዳወከ ሁሉ ለሥርዓትና ደንብ አንገዛም ባዮችን ዕንቅልፍ ነስቷል። ድርጅቱ በአካል ባይኖርም መንፈሱ እንቅልፍ የነሳቸው እነኝህ ወገኖች ባገኙት ዘዴ ሁሉ ቅሪቱን ለመመረዝ ታግለዋል - ስሙን ፣ አርማውን ጭምብል ለማድረግ ጥረዋል።

የቅንጅትን መንፈሰ ለማርከስና እስከ መጨረሻው ማክተሙን ለራሱ ለማረጋገጥ ሲል ወያኔ አንዴ የነ ጫሚሶ ቅንጅት ፣ ሌላ ግዜ የነ ልደቱ አርማ እያለ የመቀበሪያ ሳጥኑን ሚስማር ደህና አድርጎ ቀርቅሯል። ለሰላማዊ የትግል አማራጭ የቆመው ቅንጅት ብዙ ምርጫ አልነበረውም። ቅንጅትን ከሞት ለማትረፍ ታሪክ ዕድል የሰጣቸው አንዳንድ መሪዎቹ በበኩላቸው ህመሙን ሲያባብሱ ፣ ሞቱን ሲያቀላጥፉ እንጂ የዲሞክራሲን ፈለግ ተከትለው ሊታደጉት ሲሞክሩ ፣ በጠረጴዛ ዙርያ መክረው ችግራቸውን ሲያቃልሉ አላየንም። ይልቁንም ሽምግልና ይየው ፣ መንፈሳዊ አባቶች ይዳኙን ያሉ አባላትና መሪዎች ተንቀው ፣ ተሸርድደወ ጉዳዩ እንደማይሆን ሆኗል። የዚህ ሁሉ አጠቃላይ ድምር ውጤት ቅንጅት የሚባል ድርጅት እንደሌለ ቁልጭ አድርጎ የሚያመለክት ይመስለኛል። መራራው እውነት ይኼ ነው።

ቅንጅት በዜጎች ልቦና ውስጥ የተጎናፀፈውን ክብር በንግድ ምልክትነት ወይም የሥልጣን ፍላጎት ማረጋገጫ ለማድረግ መሞከር አትራፊ ቢመስልም በጥንቃቄ እና በአግባቡ ካስተዋሉት ግን አደጋ እንዳለው መገንዘብ ያስፈልጋል። መኢአድ በቶርንቶ ነበረ ፣ አሁንም አለ - የንግድ ምልክቱ ግን ቅንጅት አይደለም። መኢአድ እና ቅንጅት እንደ ዱባና ቅል አበቃቀላቸው ለየቅል ነው። መኢአድ በተለያዩ የፖለቲካ እና የፓርቲ አደረጃጀት ጥያቄዎች ላይ ያለውን አቋም እዚህ በመተንተን ከቅንጅት መሠረታዊ አቋሞች ጋር ምን ያህል እንደሚጣረስ ለማሳየት ግዜ አላባክንም። የውጭው ነዋሪ ቅን ኢትዮጵያዊ ጉዳዩን ጠንቅቆ የሚያውቀው በመሆኑ ተጨማሪ ማብራሪያ የሚያሻው ጉዳይ አይመስለኝም።

እርግጥ የመኢአድን ፖለቲካዊ አቋም በሚመለከት እራሱን የቻለ ሰፊ ትንተና ማድረግ ቀላል ቢሆንም ወቅቱ ከሚጠይቀው ትግል እና ትኩረት አንፃር ዛሬ ይህን ትንትና በማቅረብ የሚገኝ ፖለቲካዊ ትርፍ ስለሌለ ወደዚያ አልሄድም።

ባጭር አገላለፅ ግን ቅንጅት ግልፅነትን ፣ አሳታፊነትን እና ተጠያቂነትን የማዕዘን ድንጋይ አድርጎ የቆመ ድርጅት ነበር። ያንን የቅንጅት መርህ በመቀበል ፣ ዜጎች በመላ ፣ በተለይም በውጭው አለም የተበተነው ኢትዮጵያዊ በሚኖርበት ክልል ሁሉ የድጋፍ ቻፕተሮች በራስ አነሳሽነት ጭምር በማቋቋም ሁለገብ ድጋፍ አበርክቷል። የትግሉም ሆነ የድጋፉ ትኩረት - በኢትዮጵያ ሰላማዊ ዲሞክራሲያዊ የመንግስት ለውጥ ሥርዓት ለዘለቄታው እንዲተከል የሚያስችል ለውጥ ለማምጣት ነበር። ጥረቱ በጠመንጃ ተመክቶ የፖለቲካ ሥልጣን መጨምደድ እንዲያበቃ ካለው ፅኑ ምኞት የመነጨ ድጋፍ ነበር። ጥረቱ ፣ በከፋፍለህ ግዛ የጎጥ ፖለቲካ ቀምበር ሥር የወደቀችውን አገር ለመታደግ እና የሁሉም ዜጎች ሰብአዊ መብት በህግ የበላይነት የተረጋገጠባት አገር እንዲኖረን ካለው ፅኑ ምኞት የመነጨ ድጋፍ ነበር። ጥረቱ ጠለቅ ያለ ብሔራዊ እንድምታ ያለው ፣ ለዛሬው ብቻ ሳይሆን ለተከታታይ ትውልድ መመኪያ ፣ እፎይታ የሚሆን ፍትሀዊ የፖለቲካ ሥርዓት ማቆየት ተገቢ መሆኑን ከማመን የመነጨ ፍላጎት ነበር።

የትግሉ ፣ የድጋፉም ሆነ የድሉ ሚዛን የሚለካው ከነኝህ እና ከመሳሰሉት ውጤቶች አንፃር መሆን ይኖርበታል የሚል ብርቱ አቋም አለኝ። የቶሮንቶው “መኢአድ/ቅንጅት” ባሰራጨው የድል ብሥራት ላይ እንዳቀረበው ግን ላለፉት ሶስት ዓመታት ፍርድ ቤት ሲሟገት የቆየው ከወያኔ ጋር አልነበረም ፣ ከጎጠኞች ጋርም አልነበረም። ሙግቱ እና ድሉ መኢአድ ካልሆኑ ነገርግን ቅንጅትን እንደ ቅንጅት ለመደገፍ እራሳቸውን ካሰባሰቡ ቅን ኢትዮጵያዊያን ዜጎች ጋር ነበር።

መኢአድ እነኝህን ቅን የቅንጅት ደጋፊ ሀይሎች በካናዳ ፍርድ ቤት ሲሞግት ሶስት አመት ቆጥሯል። ብዙ ግዜ አባክኗል ፣ ለጠበቃ እና ፍርድ ቤቶች ብዙ ገንዘብ ተከፍሏል (ባክኗል)። የልጆቿን አንድነት ከምንግዜውም በላይ በምትሻው ኢትዮጵያ ፊት ጥላቻ እና ቂም በአንዲት አገር ዜጎች መካከል እንዲስፋፋ ሆኗል። መኢአድ ይህን የጥፋት ሤራ እንደ ‘ድል’ ቆጥሮት ጮቤ ረግጧል። መኢአድ እንደ ድርጅት ለዚህ ወራዳ ድርጊት ተጠያቂ ነው።

የመኢአድ መሪ አቶ ሀይሉ ሻውል የዚህን ክስ ሂደት አስመልክቶ የተዛባ እና የሚቃረን አቋም ሲያንፀባርቅ እንደነበር እናስታውሳለን። አንድ ግዜ ‘ተቻችለው ፣ አብረው መሥራት ካልቻሉ ሁሉም እርባና የላቸውም’ ሲል ብንሰማም ፣ ሌላ ግዜ ደግሞ ‘ክሳችን ተጠናክሮ እስከመጨረሻው ይቀጥላል’ በማለት ንትርኩን ሲያበረታታ እንደነበር ይታወቃል። የአቶ ሀይሉ አቋም የድርጅቱ አጠቃላይ ገፅታ ነፀብራቅ መሆኑን የሚጠራጠር ያለ አይመስለኝም።

አንድ ድርጅት የሚቋቋምበት መሠረታዊ ተጨባጭ ምክንያት አለው። ብዙውን ግዜ የፖለቲካ ድርጅቶች የሚመሠረቱት የህዝብን ጥያቄ እና ፍላጎት ምርኩዝ አድርገው ነው። በዚህ መልኩ የተቋቋሙ የፖለቲካ ድርጅቶች ድላቸውም ሆነ ሽንፈታቸው ፣ መስዋዕትነታቸው ሆነ እርምጃቸው ከህዝብ ፍላጎት እና ስሜት ጋር አብሮ የሚሄድ ነው። ድላቸው የህዝብ ድል ነው። ሴራ እዚህ እና እዚያ መቋጠር ይቻላል ፣ ሌሎች ላይ ደባ መፈፀም ቀላል ነው። ይህ ግን ከህዝባዊ ድል ተራ የሚገባ ጉዳይ አይደለም።

ቅንጅት የተመሠረተው ለአንድ እና ለአንድ አላማ ብቻ ነበር። መርሆው ምን እንደነበር ከፍ ሲል ጠቅሻለሁ - የቅንጅት ድል የመላ ኢትዮጵያ ህዝብ ድል ነበር። ህዝብ የሥልጣን ምንጭ እና ባለቤት መሆኑን የሚያረጋግጥ የፖለቲካ ሥርዓት እስካልተረጋገጠ ድረስ የቅንጅት መንፈስ ከድል ማማ ላይ ቆምያለሁ ቢል እራስን ከመሸንገል በቀር ሌላ ሊሆን አይችልም። ይህ ደግሞ በየጓዳው እየተሯሯጡ ፣ በፍርድ ቤት እየተመላለሱ ቀላጤ በማርቀቅ የሚገኝ ድል አይደለም። ለህዝብ አንድነት እና ለአገር ደህንነት ቅድሚያ ሰጥቶ በማያሻማ የዲሞክራሲያዊ መርሆ ላይ የተገነባ ትግል ማድረግን ይጠይቃል።

የኢትዮጵያ ህዝብ ትግል መጠነ ሰፊ ነው ፣ ድሉም ያንኑ ያህል አንፀባራቂ እና ዘላቂ ሊሆን ይገባዋል። ያንን ግዙፍ የትግል ጥያቄ ተቀብሎ ለወሳኙ ድል መታገል አንድ ነገር ነው። አቀበቱን ወጥቶ ከድል ማማ ላይ ለመቆም ትንፋሽን ዋጥ አድርጎ ፣ የጠየቀውን ሁሉ ከፍሎ መሰለፍ ግድ ይላል። ከማማው ላይ ለመድረስ የሚደረገው ጉዞ ቀበቶን ጠበቅ ማድረግ ይጠይቃል። ይህን ማድረግ ከተሳነን ደግሞ ያለው አማራጭ የቶርንቶው መኢአድ እንዳደረገው ቁልቁል መንደርደር ነው። ወያኔን እና ጎጠኝነትን ሳይሆን ቅን ኢትዮጵያውያንን በፍርድ ቤት ረትቶ ‘በድል’ ጮቤ መርገጥ። ጥሬ ስጋ እና ውስኪ መራጨት። ቁልቁል መንደርደር ያን ያህል ቀላል ነው።

ለማጠቃለል ያህል - ‘የቅንጅት መንፈስ’ ያደረባቸው ሚሊየን ዜጎች አንድነቷ በተረጋገጠ አገር ሁሉም ዜጋ በህግ ፊት እኩል ሆኖ እስካላዩ ድረስ ‘ድል’ በሚል ቋንቋ ሲጫወቱ አይገኙም። እናም ከዲሞክራሲያዊ ነፃነት በመለስ የሚያስፈነድቃቸው ድል የለም። ጥያቄያቸው በፍርድ ቤት የስያሜ ሽሚያ ሳይሆን በትግሉ ጎራ ብቻ እንደሚረጋገጥ ጠንቅቀው ይረዳሉ። ይህን ሀቅ የተላበሱ መሪዎች ዛሬ ድረስ የቅንጅትን መሠረታዊ መርሆዎች አንግበው ለነፃነታችን ትግል ተገቢውን ስልት በመቀየስ ጎጠኝነትን ፊት ለፊት ተጋፍጠዋል። አቀበቱን ለመውጣት ሀሞት ይጠይቃል - በየመንደሩ አሉባልታ እያናፈሱ ለመሳለቅ የሚጠይቀው ነጭ ጥርስ እና መፋቂያ ብቻ ነው። ጥርስ እየፋቁ ቁልቁል መንደርደር።